የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን
ETHIOPIAN COMMUNICATIONS AUTHORITY

# የቴሌኮሚኒኬሽን ፈቃድ መመሪያ

# ቁጥር 792/2013

2013 ዓ.ም

# የቴሌኮሚኒኬሽን ፈቃድ መመሪያ

የቴሌኮሚኒኬሽን ሥርዓት፣ መሠረተ ልማቶች እና የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎቶች ለማካሄድ የሚያስችል ወጠታማ ቀልጣፋ የፈቃድ አሰጣጥ ሂደት ማንባት የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ መፍጠር በማስፈለጉ፤

ባለስልጣኑ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተሮችን በበላይነት መቆጣጠር የሚችልበት እንዲሁም ፈቃድን ማሻሻል፤ ሚደስ፤ ማገድ እንዲሁም ማስረዝ የሚችልበትን ማዕቀፍ ማበጀት አስፈላጊ መሆኑን በማንዘብ፤

የመደብ እና የግል ፈቃዶችን ጨምሮ ሌሎች ፈቃዶችን እንዲሁም ተያያዥ የወል ሁኔታዎችን ማየት አስፈላጊ መሆኑን በሚዳት፤

የኢትዮጵያ ኮሚኒኬሽን ባለስልጣን በኢትዮጵያ ኮሚኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148/2011 አንቀጽ 6(2)፣ 6(7)፣20(2) እና 52(4) ማስረት ይህን የቴሌኮሚኒኬሽን ፈቃድ መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ** ይህ መመሪያ "የቴሌኮሚኒኬሽን ፈቃድ መመሪያ ቁጥር 792/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ወስጥ፡፡

1) **"አመልካች"** ማለት ፈቃድ ለማግኘት ለባለስልጣኑ የሚያመለክት ሰው ነው።

2) **"ባለሥልጣን"** ማለት በአዋጁ አንቀጽ 3 የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኮሚኒኬሽን ባለሥልጣን ነው፡፡

3) **"የጥሪ ማዕከል አገልግሎት ፈቃድ"** ማለት ደንበኞች ከሦስተኛ ወገን ኤጀንሲዎች ጋር ለሚያደርጉት ማስተጋብር ሚጃ በስልክ፣ በድረ-ገጽ ወይም በኤሌክትሮኒክ ሜልዕክት (በኢሜል) ለመቀበልና ለማስተላለፍ በባለሥልጣኑ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡

4) **"የመደብ ፈቃድ"** ማለት የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ለማስጠት እና/ወይም ፍሪኩዌንሲን ለማጠቀም የግል ፈቃድ ማውጣት ሳያስፈልግ የፈቃድ መሠረታዊ ድንጋጌዎች እና ሁኔታዎችን ለሚያሟላ ማንኛውም ሰው የሚሰጥ ፈቃድ ነው።

5) **"የዳታ ማዕከል አገልግሎት ሰጭ ፈቃድ"** ማለት ለማቅናበር፣ ለማከማቸት፣ በኔትወርክ ለማያያዝ፣ ለማስተዳደር እና ለዳታ ማሰራጨት አገልግሎት የሚውል የዳታ ማዕከል ለመተግበር፣ ለማጠን፣ ለማከናወን እና ለማከራየት የሚዲዱ ተግባራትን ወይም አገልግሎቶችን እና መገልገያዎችን ለማቅረብ የሚያስችል በባለሥልጣኑ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡

6) **"የኤሌክትሮኒክ አስተዳደር አገልግሎት"** ማለት በአስተዳደር አገልግሎቶች ሳይወሰን የግብርና፣ የትምህርት እና የጤና አገልግሎቶችን ጨምሮ ማህበራዊ አገልግሎቶችን በተሰጣቸው ተልዕኮ መሠረት የኤሌክትሮኒክ አገልግሎቶችን በተሻለ ለማቅረብ በተገደበ የተገልጋዮች ጎራ በማንግስት ተቋማት የሚሰጥ ማንኛውም አገልግሎት ነው።

7) **"ቋሚ ኔትወርክ"** ማለት ለድምፅ፣ ለዳታ እና ለብሮድባንድ ኮሚኒኬሽን የሚያገለግሉ ባለገመድ ኔትወርክ ነው፡፡

8) **"ዓለም አቀፍ የሳተላይት የግል ሞባይል ግንኙነት አገልግሎት ፈቃድ"** ማለት በኢትዮጵያ ወስጥ ምንም ዓይነት መሠረተ ልማት ወይም ኔትወርክ ሳይኖር በሳተላይት የሞባይል የድምፅ ወይም የኢንተርኔት እና የዳታ አገልግሎት ለማስጠት በባለሥልጣኑ የሚሰጥ የሀገሪቱን የግዛት ወሰን የማጠቀም ፈቃድ ነው፡

9) **"የሆስቲንግ አገልግሎት ሰጪ ፈቃድ"** ማለት ኢንተርኔትን ማዕረት ያደረጉ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሀብቶችን ለተቋማት ወይም ለግለሰቦች በርቀት ለማቅረብ የሚውሉ የመተግበሪያ አገልግሎቶችን በመጠቀም በዳታ ማዕከል ወይም በኮሎኬሽን የሆስቲንግ አገልግሎት ለመስጠት በባለሥልጣኑ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡

10) **"የግል ፈቃድ"** ማለት በወድድር የፍቃድ አሰጣጥ ሂደት የሚሰጥ ፈቃድ ሲሆን በቁጥር ወሰን ለሆኑ ፈቃዶች አንድ ወይም ከአንድ በላይ ኦፕሬተሮችን ከአመልካቾች ቡድን መምረጥን ያካትታል፡፡

11) **"የወስጥ የቴሌኮሚኒኬሽን መሳለገያዎች ተከላ እና ጥገና ሥራዎች ፈቃድ"** ማለት የቴሌኮሚኒኬሽን ኬብል፣ የዳታ ኔትወርክ በመኖሪያ ቤት፣ በሕንፃ ወይም በግቢ ወስጥ ለማዘርጋት እና ለማጠገን በባለሥልጣኑ የሚሰጥ ፈቃድ ሲሆን የግል ቅርንጫፍ ማዞሪያ እና የቴሌፎን ማከፋፈያ ተርሚናል ማዘርጋትን ያካትታል።

12) **"የኢንተርኔት ማዞሪያ ማዕከል"** ማለት በዋነኛነት የኢንተርኔት ትራፊክ ልወወጥን ለማምቻቸት ዓላማ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የተለያዩ እራሳቸውን የቻሉ ሥርዓቶች እርስ በርስ እንዲተሳሰሩ የሚያስችል የኔትወርክ መሠረተልማት ነው።

13) **"የኢንተርኔት ማዞሪያ ማዕከል ፈቃድ"** ማለት እራሳቸውን የቻሉ የኢንተርኔት ኔትወርኮች የትራፊክ ልወውጥ የሚያደርጉበትን መሠረተልማት ለማቅረብ በባለሥልጣኑ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡

14) **"የዓለም አቀፍ ግንኙነት በር ፈቃድ"** ማለት ዓለም አቀፍ የድምፅ ወይም የዳታ እና የኢንተርኔት አገልግሎት ወይም የዓለም አቀፍ የማስራጨት አቅም በማይክሮዌቭ፣ በባህር ወስጥ በተዘረጋ ኬብል/ፋይበር፣ በየብስ ላይ በተዘረጋ ኬብል/ፋይበር ወይም ሳተላይት በመጠቀም እና ለድምጽ አገልግሎት የኢንተርኔት ፕሮቶኮልን በመጠቀም ድምጽን በኢንተርኔት ፕሮቶኮል ላይ የማስተላለፍ አገልግሎት ለማስጠት በባለሥልጣኑ የሚሰጥ ፈቃድ ነው።

15) **"የኢንተርኔት አገልግሎት ሰጪ ፈቃድ"** ማለት የራስን ወይም በኪራይ የተገኘን መሠረተ ልማት በመጠቀም ድምጽን በኢንተርኔት ፕሮቶኮል ማስተላለፍን ጨምሮ የኢንተርኔት ተደራሽነት ወይም አገልግሎት ለማስጠት በባለሥልጣኑ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡

16) **"አይ. ኤስ. ኤም ባንዶች"** ማለት በአለም አቀፍ የቴሌኮሚኒኬሽን ህብረት መሠረት ለተሰየሙት የኢንዱስትሪ፣ ሳይንሳዊ እና የህክምና ትግበራዎች የሚውሉ የፍሪኩዌንሲ ባንዶች ናቸው።

17) **"ፈቃድ"** ማለት በባለሥልጣኑ የተሰጠ ፈቃድ ነው፡፡

18) **"ባለፈቃድ"** ማለት በባለሥልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፡፡

19) **"የሞባይል ኔትወርክ"** ማለት ማንኛውንም የሽቦ አልባ ቴክኖሎጂ ትወልድ በመጠቀም በኢትዮጵያ ወስጥ በማንኛወም ሥፍራ ድምጽ፣ ጽሁፍ፣ ዳታ እና ቪዲዮን ጨምሮ ማንኛውንም የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ለማስጠት እና የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ወደ ውጭ ሀገር ለመላክ እና ለመቀበል የሚያስችል የሴሉላር ሞባይል ኔትወርክ ነው፡፡

20) **"የውጭ የቴሌኮሚኒኬሽን መሳለገያዎች ተከላ እና ጥገና ሥራዎች ፈቃድ"** ማለት የቴሌኮሚኒኬሽን ታወሮች፣ የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ደረጃ ኬብሎች፣ የሜጨረሻ ምዕራፍ አገናኝ፣ የፋይበር ዋና ማስመር እና በአካባቢያዊ ማዞሪያ እና ግቢ መካከል ትስስር የሚፈጥሩ የፋይበር ወይም ቋሚ ገመድ አልባ ኔትወርኮችን ለመትከል እና ለማጠገን በባለሥልጣኑ የሚሰጥ ፈቃድ ነው።

21) **"የመናኛ ሬዲዮ ፈቃድ"** ማለት ለንግድ ላልሆነ የግል አገልግሎት የሚውል ቋሚ፣ ተንቀሳቃሽ እና በእጅ የሚያዝ የመናኛ ሬዲዮ አገልግሎት ለመትከል እና ለማጠቀም በባለሥልጣኑ የሚሰጥ ፈቃድ ነው።

22) **"የግል ኔትወርክ/የተገደበ ተገልጋዮች ጎራ/ አገልግሎት ፈቃድ"** ማለት ፈቃድ ካለው የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት በማግኘት የወስጥ የድርጅት ዳታ፣ የድምጽ እና የቪዲዮ ትራፊክ ለማስተላለፍ በተገደበ የተገልጋዮች ጎራ በኢትዮጵያ ወስጥ ለማስራት እና ለማጠቀም በባለሥልጣኑ የተሰጠ ፈቃድ ነው።

23) **"አዋጅ"** ማለት በተለየ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር፣ የኮሚኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148/2011 ነው፡፡

24) **"የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ፈቃድ"** ማለት በሀገር አቀፍ ደረጃ ወይም በተወሰነ ሚኦግራፊያዊ ክልል የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም የተወሰነ ክፍል የቴሌኮሚኒኬሽን፣ የብሮድካስቲንግ ወይም ማንኛውም ሌላ የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ለማስጠት ወይም በግል ለማጠቀም በባለሥልጣኑ የሚሰጥ ፈቃድ ነው።

25) **"የሳተላይት ዜናዎች ማሰብሰቢያ አገልግሎት ፈቃድ"** ማለት የሳተላይት ዜናዎች ማሰብሰቢያ መሣሪያ ለማጠቀም በባለሥልጣኑ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡

26) **"የተጣማሪ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ፈቃድ"** ማለት የማሪያ ኔትወርኮችን ጨምሮ በሚያላለፉበት መንገድ (የሽቦ ማሰሚር – መዳብ፣ ፋይበር፣ ኬብል፣ ገመድ አልባ፣ ሳተላይት) ሳይገደብ፣ የአለምአቀፍ በር፣ የኢንተርኔት ልወውጥ እና ማንኛውንም የኤሌክትሮኒክ ኮሚኒኬሽን አገልግሎቶች ለማስጠት በሚያስችል ቴክኖሎጂ የኢንተርኔት ቴሌፎንን ጨምሮ ደምጽ፣ ዳታ፣ ጽሁፍ እና ቪዲዮ የቴክኖሎጂ እና የአገልግሎት ገለልተኝነት መርሆችን በተከተለ ሚሉኩ በኢትዮጵያ ወስጥ ማንኛውንም የሞባይል እና ቋሚ ኔትወርኮች በማንኛውም ስፍራ ለማቅድ፣ ለማንባት፣ ለማከናወን እና ለማስቀጠል እና የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ወደ ውጭ ሀገር ለመላክ እና ለመቀበል በባለሥልጣኑ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡

27) **"የቴሌኮሚኒኬሽን ተጨማሪ አገልግሎቶች ፈቃድ"** ማለት የቴሌኮሚኒኬሽን ኔትወርክ አቅራቢዎች ዋነኛ አገልግሎት ያልሆኑ የሞባይል፣ የኢንተርኔት ወይም የመደበኛ የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ተጨማሪ አገልግሎቶች እና ፕሪሚየም ደረጃ የተሰጣቸው አገልግሎቶችን ጨምሮ ለማቅረብ በባለሥልጣኑ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡

28) **"የቪሳት አገልግሎት ፈቃድ"** ማለት አንድ ባለፈቃድ እርስ በርስ ለተገናኙ የራሱ ተጠቃሚዎች ብቻ ለንግድ ላልሆነ ዓላማ የቪሳት መሳሪያ ተክሎ ለማጠቀም በባለሥልጣኑ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡

29) **"የመሠረተልማት አቅርቦትን ያላካተተ የኢንተርኔት አገልግሎት አቅርቦት ፈቃድ"** ማለት ከተጣማሪ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ባለፈቃድ ወይም የኢንተርኔት አገልግሎት ሰጪ ባንድዊድዝ ወይም የኢንተርኔት ኔትወርክ መሣሪያ በመከራየት ለደንበኞች የኢንተርኔት አገልግሎት ለማቅረብ በባለሥልጣኑ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡

30) **"የሥራ ቀናት"** ማለት ሥራ የሚከናወንባቸውን የሥራ ቀናት ብቻ ሲሆን ቅዳሜ እሁድ እና በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ በዓል ሆኖ የታወጀን ማንኛውንም ቀን አያካትትም።

**3. ዓላማ**

የዚህ መመሪያ ዓላማ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ደሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ወስጥ የቴሌኮሚኒኬሽን ሥርዓት፣ መሠረተ ልማቶች እና የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎቶች ለማካሄድ የሚያስችል የአሰራር ስርሃት ማዘርጋት እንዲሁም ለቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ወጠቃሚና ቀልጣፋ የፈቃድ አሰጣጥ ሁኔታ መፍጠር የሚያስችል ሜቀፍ መፍጠር ነው፡፡

**4. የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በሚከተሉት የፈቃድ ዓይነቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፤

1) የግል ፈቃድ፤

2) የመደብ ፈቃድ፤

3) የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም እና የመገናኛ ሬዲዮ ፈቃዶች፤ እና

4) በባለሥልጣኑ የሚወሰንና የሚወጣ ማኝናወም ሌላ የፈቃድ ዓይነት፡፡

## ክፍል ሁለት

## የፈቃድ አስፈላጊነት፣ ሂደት እና ከፈቃድ ነፃ መሆን

### 5. የፈቃድ አስፈላጊነት

1) ማንኛውም ሰው በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ መሠረት ፈቃድ ሳያገኝ ወይም ከባለስልጣኑ ከፈቃድ ነጻ የመሆን መብት ሳይሰጠው የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ማቅረብ ወይም የኔትወርክ አገልግሎት ማካሄድ አይችልም፡፡

2) ማንኛውም ሰው በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ መሠረት ከባለስልጣኑ የተሰጠ ፈቃድ ሳይኖረው የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ማጠቀም አይችልም፡፡

3) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) ቢኖርም በአንዳንድ የተወሰኑ የፍሪኩዌንሲ ባንዶች ውስጥ ያሉ ተጠቃሚዎች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 መሠረት በባለሥልጣኑ በግልጽ በሚወሰነው መሠረት ፈቃድ ከማውጣት ነጻ ሊሆኑ ይችላሉ።

4) በለሥልጣኑ ከፈቃድ ነጻ የሆኑ ባንዶችን የሚጠቀሙ መሣሪያዎችን የቴክኒክ ማሳፈርት በግልጽ በማሳየት ከፈቃድ ነጻ ሠንጠረዥ ማዘጋጀት አለበት።

### 6. ከፈቃድ ነፃ ስለመሆን

1) የዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ቢኖርም፣ ባለሥልጣኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር ግልጽ ምክክር በማድረግ የተወሰኑ የተሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች ወይም የኅብረተሰብ ክፍል ፈቃድ ከማውጣት ግዴታ ነፃ የማድረግ ትእዛዝ ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

2) ከፈቃድ ነጻ ማድረግ ተለይተው የተገለጹ ማህበረሰቦችን እንዲሁም ለትርፍ ያልተቋቋሙ እና / ወይም የማህበራዊ–ዓላማ ድርጅቶችን ከቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች ጋር ለማገናኘት አላማ ያደረጉ ሰዎች ፍላጎት ምላሽ ማስጠት አለበት፡፡ ለዚህ ዓላማ አንድ ማህበረሰብ ልዩ ባህሪዎች እና የጋራ ፍላጎቶች ያላቸው በአንድ ተመሳሳይ መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ የሚኖሩ ሰዎችን ስብስብ ማካተት አለበት፡፡

3) ከፈቃድ ነጻ ማድረግ ለወታደራዊ፣ ለፖሊስ፣ ለብሔራዊ ደህንነት እና ለኤሌክትሮኒክ አስተዳደር የሚውሉ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶችን ማካተት አለበት።

4) ባለሥልጣኑ ከፈቃድ ነጻ የማድረግ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ በአዋጁ አንቀጽ 20(4) በተደነገጉ መርሆዎች መመራት አለበት።

5) ባለሥልጣኑ ከፈቃድ ነፃ የማድረግ ትእዛዝ ከማስጠቱ በፊት የሚሰጠው አገልግሎት በቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰጪዎች ወይም ደንበኞች ላይ ጣልቃ የሚገባ ወይም ጉዳት የማያደርስ መሆኑን ሚረጋገጥ አለበት፡፡

### 7. የፈቃድ ወሰን

1) በባለሥልጣኑ የሚሰጥ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰጪ ፈቃድ ባለፈቃዱ የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ ባለቤት እንዲሆንና ስራውን እንዲያካሄድ እና/ወይም በፈቃዱ በተመለከቱት ሁኔታዎችና ደንቦች መሠረት የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት እንዲሰጥ የሚፈቅድ መሆን አለበት፡፡

2) ባለፈቃዱ በፈቃዱ ውስጥ በግልጽ ያልተመለከቱ ማናቸውንም አገልግሎት ማስጠት ወይም ስርዓትን ማስተዳደር አይችልም፡፡

3) ፈቃድ የሚጠየቅበት መሆኑ ያልተገለፀ አገልግሎት የሚሰጥ ወይም ስርዓት የሚያስተዳድር ማንኛውም ሰው አገልግሎቱን ማጠት ወይም ስርዓቱን ማስተዳደር ፈቃድ የሚያስፈልገው መሆኑ ከተገለፀ ፈቃዱን እስከሚያገኝ ድረስ ባለሥልጣኑ በሚያስቀምጣቸው ሁኔታዎች እና ደንቦች አገልግሎት ማጠቱን ወይም ስርዓት ማስተዳደሩን ሊቀጥል ይችላል፡፡

## 8. የፈቃድ ማመልከቻ ሁኔታዎችና መስፈርቶች

1) የፈቃድ ማመልከቻው ተቀባይነት የሚኖረው አመልካቹ፤

ሀ) በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ወስጥ በሥራ ላይ ባለ የንግድ ምዝገባ እና ፈቃድ እና/ወይም የኢንቨስትመንት ሕግ መሠረት የተመዘገበ ከሆነ፤

ለ) በፈቃዱ መሠረት ሥራወን ለማከናወን በባለሥልጣኑ የወጣወን የቴክኒክ መስፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ፤

ሐ) የቴሌኮሚኒኬሽን ኔትወርክ ለማዘርጋት እና ስራወን ለማካሄድ ወይም/እና ባለሥልጣኑን በሚያረካ ሁኔታ ዘለቄታ ያለው የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ለማስጠት የሚያስችል በቂ የፋይናንስ አቅም ያለው ከሆነ፤ እና

መ) እንደ ስፔክትረም እና ቁጥር ያሉ ወስን ሀብቶች ላይ የተመሠረተ አገልግሎት ከሆነ ባለሥልጣኑ እነዚህ ሀብቶች መኖራቸወን እና ለአመልካቹ የተመደበለት ወይም የተያዘለት መሆኑ ከተረጋገጠ፡

2) እያንዳንዱ የቴሌኮሚኒኬሽን ፈቃድ ማመልከቻ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጁ እና በባለሥልጣኑ ድረ- ገጽ ወይም ቢሮ የሚገኙ የማመልከቻ ቅጾችን በመሙላት እንዲሁም በባለሥልጣኑ የተወሰነወን የማመልከቻ ክፍያ ከተከፈለበት ማስረጃና ሌሎች በባለሥልጣኑ ለወሰኑ የሚችሉ ሰነዶችን በማያያዝ ለባለስልጣኑ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

3) ለፈቃድ የሚቀርብ ማመልከቻ ከሚከተሉት ሚጃዎች ጋር ለባለሥልጣኑ መቅረብ ይኖርበታል፤

ሀ) በባለሥልጣኑ የተገለጹ የምዝገባ ወይም የማታወቂያ ሰነዶች፤

ለ) እንደ አግባቡ የመመሥረቻ ጽሑፍና የመተዳደሪያ ደንብ፤

ሐ) እንደ አግባባቡ የባለአክሲዮኖች ስም ዝርዝር፣ ዜግነት፣ አድራሻ፣ የገዙት የአክሲዮን ብዛትና ዋጋ፤

መ) የአመልካቹ የሚልዕክት መላኪያ እና/ወይም በኢትዮጵያ ቋሚ የመኖሪያ አድራሻ፤

ሠ) እንደ አግባቡ ሊሰጥ ስለታሰበው አገልግሎት አይነት፣ ኔትወርክ እና የሚሸፍነው ቦታ ዝርዝር የያዘ የቢዝነስ ዕቅድ፤

ረ) እንደ አግባቡ አመልካቹ መመስረት እና ማካሄድ ስለፈለገው የኔትወርክና የሚከተላለፊያ ሥርዓቶች ዝርዝር መግለጫ እንዲሁም የኔትወርክ ዝርጋታ የሚከናወንበት እና ስራ የሚጀምርበት የጊዜ ሰሌዳ፤

ሸ) እንደ አግባቡ ለማካሄድ ከታሰበው ወይም ፈቃድ ከተጠየቀበት የቴሌኮሚኒኬሽን ኔትወርክ ወይም አገልግሎትጋር የተያያዙ ቀደምት የአስተዳደር ልምዶችን የሚያሳዩ ሚጃዎች፤ እና፣

ቀ) ኔትወርክ ለማዘርጋት እና ስራወን ለማካሄድ ወይም/እና ባለሥልጣኑን በሚያረካ ሁኔታ ዘለቄታ ያለው አገልግሎት ለማጠት የሚያስችል በቂ የፋይናንስ አቅም ስለመኖሩ ለሚያረጋግጥ በባለሥልጣኑ የሚጠየቁ ሚጃዎች፡፡

4) ባለሥልጣኑ ከአመልካቾች የሚሰበሰቡ ሚጃዎችን ሚስጥራዊነት ለማጠበቅ ተገቢ እርምጃዎችን መወሰድ አለበት፡፡

## 9.የፈቃድ ሁኔታዎችን ስለማሻሻል

1) ባለሥልጣኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ የአዋጁን አንቀጽ 34-37 መሠረት በማድረግ የፈቃድ ሁኔታዎች በተመሳሳይ ምድብ ወስጥ ለሚሰጡ ሁሉም ፈቃዶች ላይ የሚተገበሩ ሁኔታዎች ጋር የሚስማማ ለማድረግ እና በምድብ ወስጥ ባሉ ባለፈቃዶች መካከል ፍትሐዊ ወድድርን ለሚያረጋግጥ ዓላማ የፈቃድ ሁኔታዎችን ማሻሻል ይችላል፡፡

2) ባለሥልጣኑ ማቸወንም የፈቃድ ሁኔታዎችን ለማሻሻል ሲያቅድ ለሁሉም ባለፈቃዶች፤

ሀ) ስለታቀደው ማሻሻያ ምክንያቶች፤ እና፣

ለ) የታቀደው ማሻሻያ ተግባራዊ ስለሚሆንበት ቀን፤

በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

3) ባለፈቃዱ የጽሑፍ ማስታወቂያው በደረሰው ስልሳ (60) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ወስጥ ሃሣቡን በጽሑፍ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ ይችላል፡፡

4) በታቀደው ማሻሻያ ላይ የሚጨሻ ወሳኔ ከመተላለፉ በፊት ባለሥልጣኑ ግልጽ እና በምክከር ላይ የተመሠረተ ሂደት በማካሄድ ማሻሻያው ተፅዕኖ ከሚየሳርፍባቸው ባለፈቃዶች ወይም ማንኛውም ፍላጎት ካለው አካል የቀረቡ ሃሳቦችን ከግምት ወስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡፡

## 10. በባለሥልጣኑ ስለሚጠየቁ ተጨማሪ ሚጃዎችና ሰነዶች

1) ባለሥልጣኑ ፈቃድ ለማግኘት የቀረበለትን ማመልከቻ ከተቀበለ በኋላ በማቸወም ጊዜ አመልካቹ ለማመልከቻው ደጋፊ የሆኑ ተጨማሪ ሚጃዎችና ሰነዶች እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

2) የተጠየቁትን ተጨማሪ ሚጃዎችና ማስረጃዎች በሠላሳ (30) የሥራ ቀናት ወስጥ አለማቅረብ ማመልከቻውን እንደመተው ይቆጠራል፡፡

3) ከማመልከቻው ጋር በተያያዘ የሚቀርብ ማቸወም ሚጃ ትክክለኛ መሆን ይኖርበታል፡፡ ባለሥልጣኑ በአመልካቹ የቀረበ ማቸወም ሚጃ ወይም ሰነድ ትክክለኛ አለመሆኑን ያረጋገጠ እንደሆነ ባለፈቃዱ በሠላሳ (30) የሥራ ቀናት ወስጥ ሚጃውን ወይም ሰነዱን እንዲያስተካክል ዕድል ይሰጠዋል፡፡ ሚጃውን ማስተካከል አለመቻል እና/ወይም የተጠየቀውን ሚጃ ወይም ሰነድ አለማቅረብ ማመልከቻውን ወድቅ ማድረግን ያስከትላል፡፡

## 11. የተደረጉ ለወጦችን ለባለሥልጣኑ የማሳወቅ ግዴታ

ማመልከቻው ተቀባይነት ካገኘ በኋላ ባለፈቃዱ ድርጅቱን የተመለከቱ ዝርዝሮች፣ የቴሌኮሚኬሽን ኔትወርክ እና/ወይም የሚሰጠው አገልግሎት እና ወሰን መግለጫ ወይም ለባለሥልጣኑ የቀረቡ ማቸወም ሚጃዎች ላይ ለወጥ ካደረገ ወይም ስህተት ካገኘ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

## 12. በሥራ ላይ ያሉ ፈቃዶች

1) በሥራ ላይ ያለን ፈቃድ የያዘ ሰው ባለሥልጣኑ የሚያወጣውን የማስተቻ ስልቶች መሠረት በማድረግ በዚህ መመሪያ መሠረት ማመልከት እና አዲስ ፈቃድ ማግኘት አለበት ፡፡

2) ነባሩ የቴሌኮሚኬሽን ኦፕሬተር በዚህ መሚያ በተደነገገው መሠረት ማመልከት እና አዲስ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

3) በማመልከቻው ወቅት ነባሩ የቴሌኮሚኬሽን ኦፕሬተር በባለሥልጣኑ በሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ማጠቃሚ ክፍያ መመሪያ ወስጥ የተወሰነውን የፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ክፍያ ሚፈጸም ይጠበቅበታል፡፡

4) የዚህ መመሪያ ንዑስ-አንቀጽ (2) ቢኖርም አዲሱ የነባር የቴሌኮሚኬሽን ኦፕሬተር ፈቃድ፦-

ሀ) ያለወድድር የሚሰጥ፤ እና፣

ለ) የፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም እንደገና በመመደብ ላይ

የተመሰረተ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የግል ፈቃዶች

### 13. የግል ፈቃዶችን የሚሰጫ ዘዴዎች

1) የግል ፈቃድ የሚጠየቅባቸው የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎቶች በዚህ መመሪያ አባሪ "ሀ" ላይ የተዘረዘሩት መሆን አለባቸው፡፡

2) ባለሥልጣኑ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ዘዴዎች በመጠቀም የግል ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፤

ሀ) በጨረታ፤

ለ) በንጽጽር ወድድር፤

ሐ) ጨረታንና የንጽጽር ወድድርን በማቀላቀል፤ ወይም

መ) ባለሥልጣኑ ተገቢ ነው በሚለው በሌላ ማናቸውም ዘዴ፡

3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና የዚህ መመሪያ አንቀጽ 8፣ 9 እና 10 ቢኖሩም፣ የተጣመረ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር የግል ፈቃድን በተመለከተ ጥቅም ላይ የሚውሉ ዘዴዎችና ተዛማጅ የፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓቶች በወድድር ላይ በተመሠረተ ምርጫ የሚከናወን ሆኖ የፈቃድ ማመልከቻ በሚጠየቅበት የሕዝብ ማስታወቂያ ወስጥ የሚወሰን ይሆናል፡፡.

### 14. ለግል ፈቃድ ወሳኔ ሚሰጥበት ጊዜ

1) ባለሥልጣኑ ማመልከቻው በደረሰው ሠላሳ (30) የሥራ ቀናት ወስጥ የግል ፈቃዱ የሚሰጥ መሆን አለመሆኑን በመወሰን ለአመልካቹ ወሳኔወን በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

2) ባለሥልጣኑ ወሳኔ የሚሰጥበትን ጊዜ የሚያዘም መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ ሆኖም ጊዜው ከስልሳ (60) የሥራ ቀናት መበለጥ የለበትም፡፡

### 15. ማመልከቻን ስለማስተናገድ

1) ባለሥልጣኑ ማመልከቻው የተሟላ መሆኑን ካረጋገጠ ለተጠየቀው ፈቃድ ተፈጻሚ የሚሆኑ ሁኔታዎችን በማስፈር የማስተናገጃ ደብዳቤ ለአመልካቹ መላክ አለበት፡፡

2) አመልካቹ የማስተናገኛ ደብዳቤ በደረሰው በስልሳ (60) የሥራ ቀናት ወስጥ ተገቢወን የፈቃድ ክፍያ ማከፈል አለበት፡፡

### 16. በሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክተረም ላይ የተመሠረተ የግል ፈቃድ

በሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ላይ ለተመሠረተ አገልግሎት ፈቃድ ሲሰጥ፤

1) ፈቃዱ ለተጣመረ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር ወይም ባለሥልጣኑ ለአመልካቹ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም እስካልመደበለት ድረስ በራሱ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም እንደተመደበለት አያስቆጥርም፤ እንዲሁም፤

2) በዚህ መመሪያ ክፍል አምስት የተመለከቱትን የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ምደባ ማስፈርቶች መሟላት በቅድመ ሁኔታነት ታሳቢ የሚደረግ ይሆናል፡፡

### 17. የግል ፈቃድ ዘመንና ማብቂያ ጊዜ

1) በዚህ መመሪያ መሠረት የተሰጠ የግል ፈቃድ ለአስራ አምስት (15) ዓመት የጸና ይሆናል፡፡

2) የግል ፈቃድ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 18 በተደነገገው መሠረት ካልታደሰ በስተቀር የፈቃዱ ጊዜ ማብቃት አለበት፡፡

3) የግል ፈቃዱ የአገልግሎት ጊዜውን ጨርሶ የተቋረጠ እንደሆነ፣ ባለሥልጣኑ በጊዜያዊነት አገልግሎት ማስጠቱን እንዲቀጥል ካልፈቀደለት ወይም ካላደረገው በስተቀር የግል ባለፈቃዱ የፈቃድ ጊዜው ወይም ዘሙ እንዳበቃ አገልግሎት ማስጠቱን ወዲያውኑ ማቋረጥ አለበት፡፡

## 18. <u>የግል ፈቃድን ስለማደስ</u>

የግል ፈቃድ፤

1) የፈቃድ ጊዜው ከማብቃቱ ከስድስት (6) ወር በፊት አመልካቹ አስፈላጊ የፈቃድ ዕድሳት ክፍያ በሚፈጸም የፈቃድ እደሳት ማመልከቻ ካስገባ፤

2) ባለፈቃዱ የፈቃድ ግዴታዎችን ካሟላ እና አስፈላጊውን የማመልከቻ ቅጽ ሞልቶ ካቀረበ፤ እና

3) ባለሥልጣኑ ማመልከቻውን አጥጋቢ ሆኖ ካገኘው፣

ሊታደስ ይችላል፡፡

## 19. <u>የግል ፈቃድን ስለመመለስ</u>

1) የፀናና በሥራ ላይ ያለ የግል ፈቃድን ለመመለስ የፈለገ ባለፈቃድ፤

ሀ) ከጽሑፍ ማስታወቂያ ማስጫው ቀን ወይም ፈቃዱን ለመመለስ ከወሰነበት ቀን በፊት የግል ፈቃዱን ለመመለስ ፍላጎት እንዳለው ከአንድ (1) ዓመት ያላነሰ የቅድሚያ ማስታወቂያ ለባለስልጣኑ ማስጠት፤

ለ) ለባለፈቃዱ ደንበኞች ፈቃዱን ለመመለስና አገልግሎቱን ለማቋረጥ ፍላጎት እንዳለው ከስድት (6) ወር ያላነሰ ማስታወቂያ ማስጠቱን የሚያሳይ የጽሑፍ ማስረጃ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ፤

ሐ) ከፈቃድ መመለሻው ቀን በፊት ደንበኞቹን ለሌላ ባለፈቃድ ለማስተላለፍ ያደረገውን ዝርዝር ዝግጅቶች ለባለሥልጣኑ ማቅረብ፤ እና፣

መ) በደንበኞቹ የተፈጸሙ የቅድሚያ ክፍያዎችን ለመመለስ ዋስትና የሰጠበትን ሰነድ ማቅረብና ለሌላ ማንኛውም ባለፈቃድ ወይም ደንበኞች ምንም ዓይነት ያልተፈጸሙ ግዴታዎች እንደሌለበት ሚያጋግጥ፤

አለበት፡፡

2) ባለሥልጣኑ ፈቃዱን ለመመለስ የቀረበውን ማመልከቻ ለመመርመር አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ተጨማሪ ሚጃ ወይም ዋስትና የመጠየቅ ሥልጣን አለው፡፡

3) ባለሥልጣኑ ፈቃድ የመመለሻውን ጊዜ ለማራዘም በባለፈቃዱ የቀረበን ማመልከቻ ሊቀበል ይችላል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የሚዲብ ፈቃዶች</u>

## 20. <u>የሚዲብ ፈቃዶች ማመልከቻ</u>

1) ለሚዲብ ፈቃድ የማቅርብ ማመልከቻ አግባብ ያለውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ከአስፈላጊ ሰነዶች ጋር ተገቢውን ክፍያ በሚፈጸም ለባለሥልጣኑ መቅረብ አለበት፡፡

2) የሚዲብ ፈቃድ የሚጠየቅባቸው የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎቶች በዚህ መመሪያ አባሪ "ለ" ላይ የተዘረዘሩት መሆን አለባቸው፡፡

## 21. <u>ወሳኔ ለማስጠት ስለሚያስፈልግ ጊዜ</u>

1) ባለሥልጣኑ ሚልከቻውን በተቀበለ በሠላሳ (30) የሥራ ቀናት ወስጥ የሚዲብ ፈቃድ ማስጠት ያለበት መሆን ወይም አለመሆኑን በመወሰን ወሳኔውን በጽሑፍ ለአሚልካቹ ማሳወቅ አለበት፡፡

2) ባለሥልጣኑ ወሳኔ የሚሰጥበትን ጊዜ የማራዘም መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ሆኖም ጊዜው ከስልሳ (60) የሥራ ቀናት መብለጥ የለበትም፡፡

## 22. የመደብ ፈቃድ ዘመንና ማብቂያ ጊዜ

1) በዚህ መመሪያ መሠረት የሚሰጠው የመደብ ፈቃድ በፈቃድ ሁኔታዎች ወስጥ በሌላ ሚሁኔ እስካልተገለጸ በስተቀር ለአስራ አምስት (15) ዓመት የጸና ይሆናል፡፡

2) የግል ፈቃድ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 23 በተደነገገው መሠረት ካልታደሰ በስተቀር የፈቃዱ ጊዜ ማብቃት አለበት

3) የመደብ ፈቃዱ የአገልግሎት ዘመኑን ጨርሶ የተቋረጠ እንደሆነ፣ ባለሥልጣኑ በጊዜያዊነት አገልግሎት ማስጠቱን እንዲቀጥል ካልፈቀደለት ወይም ካላደረገው በስተቀር የመደብ ባለፈቃዱ የፈቃድ ጊዜው ወይም ዘመኑ እንዳበቃ አገልግሎት ማስጠቱን ወዲያውኑ ማቋረጥ አለበት፡፡

## 23. ስለመደብ ፈቃድ ዕድሳት

1) የመደብ ፈቃድ በፈቃድ ሁኔታዎች ወስጥ በሌላ ሚሁኔ እስካልተገለጸ በስተቀር፡-

ሀ) የፈቃድ ጊዜው ከማብቃቱ ከአስራ ሁለት (12) ወር በፊት አመልካቹ አስፈላጊውን የፈቃድ ዕድሳት ክፍያ በሚፈጸም የፈቃድ እድሳት ማመልከቻ ካስገባ፤ እና፣

ለ) ባለፈቃዱ የፈቃድ ግዴታዎችን ካሟላ፤

ለአስራ አምስት (15) ዓመት ሊታደስ ይችላል፡፡

2) የመደብ ፈቃድ ባለፈቃዱ ፈቃዱን ማሳደስ ካልፈለገ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 24 ንዑስ-አንቀጽ 1(ለ)፣ (ሐ) እና (መ) ድንጋጌዎችን ማሟላት አለበት፡፡

## 24. የመደብ ፈቃድን ስለመመለስ

1) የፀናና በሥራ ላይ ያለ የመደብ ፈቃድን ለመመለስ የፈለገ ባለፈቃድ፤

ሀ) ከጽሑፍ ማስታወቂያ ማስጫው ቀን ወይም ፈቃዱን ለመመለስ ከወሰነበት ቀን በፊት የመደብ ፈቃዱን ለመመለስ ፍላጎት እንዳለው ከስድስት (6) ወር ያላነሰ የቅድሚያ ማስታወቂያ ለባለሥልጣኑ ማስጠት ፤

ለ) ለደንበኞቹ ፈቃዱን ለመመለስና አገልግሎቱን ለማቋረጥ ፍላጎት እንዳለው ከሶስት (3) ወር ያላነሰ ማስታወቂያ ማስጠቱን የሚያሳይ የጽሑፍ ማስረጃ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ፤

ሐ) ከፈቃድ መመለሻው ቀን በፊት ደንበኞቹን ለሌላ ባለፈቃድ ለማስተላለፍ ያደረገውን ዝርዝር ዝግጅቶች ለባለሥልጣኑ ማቅረብ፤ እና፣

መ) በደንበኞቹ የተፈጸሙ የቅድሚያ ክፍያዎችን ለመመለስ ዋስትና የሰጠበትን ሰነድ ማቅረብና ለሌላ ማንኛውም ባለፈቃድ ወይም ደንበኞች ምንም ዓይነት ያልተፈጸሙ ግዴታዎች እንደሌለበት ለባለስልጣኑ ሚረጋገጥ፤

ይኖርበታል፡፡

2) ባለሥልጣኑ ፈቃዱን ለመመለስ የቀረበውን ማመልከቻ ለመመርመር አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ተጨማሪ ሚጃ ወይም ዋስትና የማጠየቅ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

3) ባለሥልጣኑ ፈቃድ የመመለሻውን ጊዜ ለማራዘም በባለፈቃዱ የቀረበን ማመልከቻ ሊቀበል ይችላል፡፡

## ክፍል አምስት

## የሬዲዮ ፍሪከዌንሲ ስፔክትረም ፈቃዶች

## 25. የሬዲዮ ፍሪከዌንሲ ስፔክትረም ፈቃድ ማመልከቻና የፈቃድ ሂደት

1) የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ፈቃድ ማመልከቻ በባለሥልጣኑ የተወሰነውን የማመልከቻ ክፍያ ከተከፈለበት ማስረጃና ሌሎች በባለሥልጣኑ ሊወሰኑ ከሚችሉ ሰነዶች ጋር ከባለሥልጣኑ ድረ-ገጽ ወይም ቢሮ ከሚገኝ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ የማመልከቻ ቅጽ ተሞልቶ መቅረብ አለበት፡፡

2) ባለሥልጣኑ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ፈቃድ ማመልከቻን እንደተቀበለ፣

ሀ) ማመልከቻው የተሟላ መሆኑን ወይም ማናቸውም ተጨማሪ ሚረጃ የሚያስፈልግ መሆኑን በሰባት (7) ቀናት ወስጥ ለአመልካቹ ማሳወቅ አለበት፡፡

ለ) ማመልከቻው የተሟላ ከሆነ ለአመልካቹ ወሳኔውን በሠላሳ (30) የሥራ ቀናት ወስጥ ማሳወቅ አለበት፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከቱት ማስፈርቶች ቢኖሩም፣ ባለሥልጣኑ ወሳኔ የሚሰጥበትን ጊዜ የሚራዘም መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ ሆኖም ጊዜው ማመልከቻው ከቀረበበት ከስልሳ (60) የሥራ ቀናት መብለጥ የለበትም፡፡

4) የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) ቢኖርም ለተጣማሪ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፐሬተር የግል ፈቃድ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ፈቃዱ በሚሰጥበት ጊዜ መመደብ ወይም እንደገና መመደብ አለበት፡፡

5) የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) ቢኖርም ለአጭር ርቀት የገመድ አልባ፣ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ማላያ እና ሌሎች አነስተኛ ኃይል የአጭር ርቀት መሣሪያዎች እና አገልግሎቶች የሚውሉ በ2.4 ጊጋ ኸርዝ እና 5 ጊጋ ኸርዝ ወስጥ ያሉ የአይ. ኤስ. ኤም ባንዶች ፈቃድ አያስፈልጋቸውም.

## 26. የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ፈቃድ የማሰጫ ዘዴዎች

1) ባለሥልጣኑ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ዘዴዎች በመጠቀም የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፤

ሀ) ቀድሞ ማመልከትን መሠረት በማድረግ፤

ለ) በጨረታ፤

ለ) በንጽጽር ወድድር፤

ሐ) ጨረታንና የንጽጽር ወድድርን በማቀላቀል፤ ወይም፣

መ) በአስተዳደራዊ ምዳባ ወይም በሚልሶ ምዳባ፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም፣ በወድድር ላይ በሚሠረት ምርጫ ለሚሰጡ የተጣማሪ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፐሬተር የግል ፈቃዶች ለሁሉም አዲስ ገቢዎች ፈቃዶቹ በሚሰጡበት ወቅት ሊገኝ በሚችል ተመሳሳይ እና በቂ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ጋር መሆን አለበት፡፡

3) ለነባሩ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፐሬተር የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም በባለሥልጣኑ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም መመሪያ መሠረት ያለተወዳዳሪ ምርጫ በአስተዳደራዊ ሁኔታ እንደገና መመደብ አለበት፡፡

## 27. የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ፈቃድ ማሰጫ ማስፈርቶች

1) የዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ሰፔክትረም ፈቃድ የቀረበ ማመልከቻ ተቀባይት የሚኖረው፤

ሀ) አመልካቹ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በሥራ ላይ ባለ የንግድ ምዝገባ እና ፈቃድ እና/ወይም የኢንቨስትመንት ሕግ የተመዘገበ አካል ከሆነ፤

ለ) አመልካቹ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ለማጠቀም የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ አስተዳደር መመሪያ ወስጥ በተደነገገው መሠረት የባለሥልጣኑን ማስፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ፤

ሐ) በአመልካቹ የተጠየቀው የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም በባለሥልጣኑ በተሰጠው የግል ወይም የሚደብ ፈቃድ አገልግሎት ለማስጠት አስፈላጊ ከሆነ ወይም ለማናኛ ሬዲዮ አገልግሎት፣ ለብሮድካስት አገልግሎት ወይም ሌላ በባለሥልጣኑ ብሔራዊ የፍሪኩዌንሲ ዕቅድ መሠረት የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ምደባ የሚያስፈልገው አገልግሎት ከሆነ ፤ እና፣

መ) የሚመደብ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ያለ ከሆነ ::

2) ለሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ፈቃድ የሚቀርብ ማመልከቻ ተቀባይነት የሚዩኖረው፤

ሀ) ባለሥልጣኑ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም የሌለው እንደሆነ፤ ወይም

ለ) በባለሥልጣኑ የተጠየቁ ፈቃድ ለማስጠት የሚያስፈልጉ ሚኝዎችን አመልካቹ ማቅረብ ካልቻለ፤

ነው፡ :

3) ሁሉም የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ፈቃዶች የሚሰጡት ብሔራዊ የፍሪኩዌንሲ ምደባ ዕቅድን መሠረት በሚድረግ መሆን አለበት፡ :

28. <u>ስለሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ፈቃድ ዘመና ስለፈቃድ መቋረጥ</u>

1) ለተጣምሪ የቴሌኮሚኬሽን ኦፐሬተር ባለፈቃድ እና ለኢንተርኔት አገልግሎት ሰጪ ባለፈቃድ የተሰጠ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ፈቃዱ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለአስራ አምስት (15) ዓመት የጸና ይሆናል፡ :

2) በመመሪያው መሠረት ለማናኛ ሬዲዮ የተሰጠ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ፈቃዱ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለአንድ (1) ዓመት የፀና ይሆናል።

3) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 29 መሠረት ካልታደሰ በስተቀር የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ፈቃድ ማብቃት አለበት፡ :

29. <u>የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ፈቃድ እድሳት</u>

1) ለማናኛ ሬዲዮ ፈቃድ የተሰጠ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ፈቃድ የፈቃድ እድሳት ማመልከቻ የፈቃድ ዘመኑ ከማብቃቱ ቢያንስ ከሠላሳ (30) የሥራ ቀናት በፊት ለባለሥልጣኑ ከቀረበ ለአንድ (1) ዓመት ጊዜ ማታደስ አለበት፡ :

2) ባለሥልጣኑ በራሱ ሥልጣን ባለፈቃዱ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም አስተዳደር መመሪያን ወይም ለሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ፈቃድ የተቀመጡትን ሁኔታዎች መሠረት በሚድረግ ወጠቃማ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም አጠቃቀም ያለው መሆኑን በማምገም የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ፈቃድን ሚደስ አለበት፡ :

3) ባለስልጣኑ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ፈቃድ እድሳትን በማንኛወም አሳማኝ ቴክኒካዊ እና ህጋዊ ምክንያት ላለሚደስ ሥልጣን አለው።

4) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) ቢኖሩም፣ የተጣምሪ የቴሌኮሚኬሽን ኦፕሬተር ባለፈቃድ ጉልህ እና ተደጋጋሚ የፈቃድ ሁኔታዎች ጥሰት ካልፈጸመ በስተቀር የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ፈቃዱን ለቀጣዬ አስራ አምስት (15) ዓመት የማነደስ መብት አለው፡ :

5) ባለሥልጣኑ ለተጣምሪ የቴሌኮሚኬሽን ኦፕሬተር ባለፈቃዶች የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ፈቃድ በሚያድስበት ወቅት ለተወሰኑ ወይም ለሁሉም ለሚታደሱ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረሞች አስተዳደራዊ፣ ወድድር ላይ የተማሰረተ ወይም ጥምር የእድሳት ሂደቶችን የመተግበር መብቱ የተጠበቀ ነው፡ :

6) ለተጣምሪ የቴሌኮሚኬሽን ኦፕሬተር ፈቃድ የተሰጠ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ፈቃድ በመጀመሪያው እና በቀጣዬ የፈቃድ ዘመን ሚጨሻ ሲታደስ በባለስልጣኑ በሚወሰነው መሠረት የሚፈለገው የዕድሳት ክፍያ ሚፈጸም አለበት፡ :

30. <u>የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ፈቃድን ስለመማለስ</u>

1) የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ፈቃድን ከባለሥልጣኑ ድረገጽ ወይም ቢሮ የሚገኘ ለዚሁ ተብሎ የተዘጋጀ የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት መመለስ ይቻላል፡፡

2) የፈቃዱ መመለስ የሚፀናው የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ፈቃድ ባለቤት ፈቃዱን በራሱ ፍላጎት ተመላሽ ያደረገበትን ደብዳቤ ባለሥልጣኑ ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ ነው፡፡

3) የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ፈቃድ ተመላሽ በሚደረግበት ቀን ያልተከፈለ ለባለሥልጣኑ መከፈል የሚገባው ማናቸውም ክፍያ ለባለሥልጣኑ መከፈል አለበት፡፡

## 31. የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ፈቃድን እንዲያስረክብ ስለማድረግ

1) ባለፈቃዱ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ፈቃዱን ሳያሳድስ የቀረ እንደሆነ፣ ባለሥልጣኑ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም የፈቃድ ዘመን ማብቃቱን ለባለፈቃዱ በማሳወቅ በሠላሳ (30) የሥራ ቀናት ወስጥ ተገቢውን ክፍያ በመክፈል የፈቃድ እድሳት ማመልከቻውን እንዲያስገባ ማጠየቅ አለበት፡፡

2) ባለፈቃዱ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ወስጥ ክፍያ ሚፈጸም እና የፈቃድ ዕድሳት ማመልከቻውን ማስገባት ያልቻለ እንደሆነ፣ ባለሥልጣኑ ፈቃዱን እንዲያስረክብ ማሳወቅ አለበት፡፡

3) በርክክቡ ጊዜ ለሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም የሚከፈለው ክፍያ የፈቃድ ዘመኑ ባበቃበት ጊዜ መከፈል የሚገባው ክፍያ መሆን አለበት፡፡

## 32. የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም አጠቃቀም

1) ባለፈቃዱ በባለሥልጣኑ የተመደበለትን የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም በሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም አስተዳደር መመሪያ በተደነገገው መሠረት ወጤታማ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ ማዋሉን ሚረጋገጥ አለበት፡፡

2) ባለሥልጣኑ ለባለፈቃዱ የተመደበውን የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም አጠቃቀም የመገምገም ሥልጣን አለው፡፡

# ክፍል ስድስት

## ፈቃድ ስለማስረዝና ስለማገድ

## 33. ፈቃድን ስለመሠረዝ

1) ባለፈቃዱ የዚህን መመሪያ ማናቸውም ድንጋጌዎች ተላልፎ ከተገኘ፣ ባለሥልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 52 ድንጋጌዎች መሠረት ፈቃዱን መሠረዝ ወይም የገንዘብ ቅጣት መጣል ይችላል፡፡

2) ባለሥልጣኑ ፈቃድ ለማስረዝ በሚወስንበት ጊዜ የሚከተሉትን ማጤን አለበት፡-

ሀ) የጥፋቱን ባህሪ እና ክብደት፤

ለ) የጥፋቱ ወጤት፤

ሐ) ጥፋቱ የተከሰተበት ሁኔታዎች፤ እና፣

መ) ጥፋቱን ለማስተካከል የተወሰዱ እርምጃዎች፡፡

3) አንድ ፈቃድ ከዚህ በታች በተመለከቱት ምክንያቶች ሊሠረዝ ይችላል፤

ሀ) ባለፈቃዱ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎችን ወይም በአዋጁ መሠረት የወጡ ሌሎች ደንቦች ወይም መመሪያዎችን ጥሶ ከተገኘ፣

ለ) ባለፈቃዱ ከፈቃዱ ጋር የተያያዙ ማናቸውንም ሁኔታዎች ጥሶ ከተገኘ እና የፈጸመውን ጥሰት ካላስተካከለ ወይም ባለሥልጣኑ ጥፋቱ እንዲስተካከል በሚወስነው ሂደት እና የጊዜ ገደብ ላይ ከባለሥልጣኑ ጋር ማስማማት ካልቻለ፤

ሐ) ባለፈቃዱ ፈቃዱ በተሰጠበት የሥራ ዘርፍ ለስድስት (6) ወራት ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ ያላደረገ እንደሆነ፤

መ) ባለፈቃዱ ፈቃድ ለማግኘት የማጭበርበር ድርጊት ከፈጸመ ወይም ለባለሥልጣኑ ወይም ለሌሎች የመንግሥት አካላት የተሳሳተ ሚጃ ከሰጠ፤

ሠ) የፈቃዱ ዘመን ካበቃና ሳይታደስ ከቀረ፤

ረ) ፈቃዱ ከተሰጠበት አላማ ወይም ሁኔታ በተጻራሪ ተግባሩን ካካሄደ፤

ሰ) ባለፈቃዱ የመክሰር ፋይል ከከፈተ፣ ንብረት ከተጣራና ድርጅቱ ከፈረሰ እና/ወይም የፋይናንስና የታማኝነት ግዴታውን መወጣት ካልቻለ፤

ሸ) ባለፈቃዱ ፈቃድ ካገኘ በኋላ በአስራ ሁለት (12) ወራት ውስጥ ሥራ ካልጀመረ ወይም የፈቃድ ግዴታዎቹን የተመለከቱትን ሁኔታዎች ማሟላት ካልቻለ፤

ቀ) ባለፈቃዱ ከሕዝብ ጥቅም ጋር በሚጋጭ ድርጊት ላይ ተሳትፎ ከተገኘ፤

በ) ባለፈቃዱ ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ሳያገኝ ፈቃዱን አስተላልፎ ወይም አከራይቶከተገኘ፤ እና

ተ) ባለፈቃዱ ፈቃዱ እንዲሰረዝ ባለሥልጣኑን ከጠየቀ፡፡

3) ባለሥልጣኑ ፈቃድ እንዲሰረዝ በሚወስንበት ጊዜ ይህንኑ ለባለፈቃዱ ማሳወቅ እና ፈቃዱን ለማሰረዝ በሰጠው ወሳኔ ላይ አስተያየቱን እንዲያቀርብ አርባ አምስት (45) የሥራ ቀናት ማስጠት አለበት፡፡

4) ባለሥልጣኑ ፈቃዱን ለመሠረዝ የሰጠውን ወሳኔ በመቃወም ባለፈቃዱ የሰጠውን አስተያየት ከግምት ወስጥ በማስገባት በአፋጣኝ የሚጨረሻውን ወሳኔ ማስጠት አለበት፡፡

5) ባለፈቃዱ በተጠቀሰው አርባ አምስት (45) የሥራ ቀናት ወስጥ ምላሽ ማስጠት ካልቻለ ባለሥልጣኑ ፈቃዱን በመሠረዝ ለባለፈቃዱ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

6) ባለሥልጣኑ ፈቃዱን ለማሰረዝ በወሰነው ወሳኔ የማይስማማ ማንኛውም ባለፈቃድ የባለሥልጣኑን ወሳኔ እንደገና እንዲታይለት ወይም በአዋጁ መሠረት ይግባኝ ማጠየቅ ይችላል ፡፡

## 34. ፈቃድን ስለማገድ

1) ባለሥልጣኑ አንድን ፈቃድ ከስድት (6) ወር ላልበለጠ ጊዜ በሚከተሉት ምክንያቶች ሊያግድ ይችላል፤

ሀ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 33 የተፈጸመ ማንኛውንም ምክንያት ለመማርመር፤

ለ) ባለሥልጣኑ የተፈጸመው ድርጊት ፈቃዱን ለመሠረዝ በቂ ምክንያት አይደለም ብሎ ካመነ፤ ሆኖም ጉድለቶቹን በተወሰነ ጊዜ ወስጥ ሚሆም ሲያስፈልግ ፡፡

2) ባለሥልጣኑ ፈቃድ ለማገድ በሚወስንበት ጊዜ ይህንኑ ለባለፈቃዱ ማሳወቅ እና ፈቃዱን ለማገድ በሰጠው ወሳኔ ላይ አስተያየቱን እንዲያቀርብ ሠላሳ (30) የሥራ ቀናት ማስጠት አለበት፡፡

3) ባለሥልጣኑ ፈቃዱን ለማገድ የሰጠውን ማስታወቂያ በመቃወም ባለፈቃዱ የሰጠውን አስተያየት ከግምት ወስጥ በማስገባት በአፋጣኝ የሚጨረሻውን ወሳኔ ማስጠት አለበት፡፡

4) የባለሥልጣኑ ወሳኔ በጽሑፍ ሆኖ ፈቃዱ የታገደበትን ምክንያት እና ባለፈቃዱ በወሳኔው በተመለተው የጊዜ ገደብ ወስጥ ጉድለቶቹን ለማስተካከል ሊወስድ የሚገባውን እርምጃዎች መጥቀስ አለበት፡፡

5) ባለሥልጣኑ ፈቃዱን ለማገድ በወሰነው ወሳኔ የማይስማማ ማንኛውም ባለፈቃድ የባለሥልጣኑን ወሳኔ እንደገና እንዲታይለት ወይም በአዋጁ መሠረት ይግባኝ ማጠየቅ ይችላል ፡፡

## 35. የፈቃድ መሠረዝና ማገድ ወጤቶች

1) ፈቃዱ የተሰረዘበት ወይም የታገደበት ባለፈቃድ የሚከተሉትን ሁኔታዎች በማሟላት ሥራውን ማቆም አለበት፡-

ሀ) ለደንበኞቹ ሥራውን ለማቆም ማሰቡን ለግል ፈቃድ ቢያንስ የስድስት (6) ወር እና ለሚዲብ ፈቃድ ቢያንስ የሶስት (3) ወር ማስታወቂያ ማስጠቱን የጽሁፍ ማስረጃ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ፤

ለ) ነባር ደንበኞችን እና ተዛማጅ ማዛገቦችን የፈቃዱ ማሰረዝ ከሚጸናበት ቀን በፊት ለሌላ ባለፈቃድ ለማዛወር የተደረጉ ዝግጅቶችን ዝርዝር ለባለሥልጣኑ ማቅረብ፤ እና፣

ሐ) ለነባር የቅድመ ክፍያ አገልግሎት ደንበኞች ገንዘብ ተመላሽ ለማድረግ ዋስትና ማስጠት እና ለማንኛውም ሌላ ባለፈቃድ ወይም ደንበኛ ያልተፈጸመ ግዴታ የሌለ መሆኑን ለባለሥልጣኑ ሚያጋገጫ ማቅረብ፡፡

2) ባለፈቃዱ ለእገዳው ምክንያት የሆነውን ማናቸውንም ድርጊት ከሚፈጸም መቆጠብ አለበት፡፡

3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም፣ ባለሥልጣኑ ባለፈቃዱ ጉዳዮቹን ለማጠቃለል ዓላማ የተወሰኑ ሥራዎችን እንዲፈጽም በጽሑፍ ሊፈቅድለት ይችላል፡፡

## 36. ፈቃድን ስለመመለስ

ተገቢ ሆኖ ሲገኝ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 33 መሠረት ፈቃዱ የተሠረዘበት ባለፈቃድ በአሥር (10) የሥራ ቀናት ውስጥ ፈቃዱን ለባለሥልጣኑ መመለስ አለበት፡፡

## 37. የጠፉ ፈቃድ

1) ተገቢ ሆኖ ሲገኝ ባለፈቃዱ ፈቃዱ የጠፋበት ከሆነ ወዲያውኑ በጽሁፍ ስለሁኔታው ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

2) ተገቢ ሆኖ ሲገኝ በባለሥልጣኑ የሚጠየቁ ሁሉንም ሰነዶች ከተወሰነው ክፍያ ጋር አብሮ በማያዝ ምትክ ፈቃድ እንዲሰጠው ባለፈቃዱ ማመልከት አለበት፡፡

## ክፍል ሰባት

## ስለፈቃድና አክሲዮኖች ማስተላለፍ ሥርዓቶች

## 38. ፈቃድን ስለማስተላለፍ ወይም ሌላ ሰው እንዲሠራበት ስለመፍቀድ

1) ባለፈቃዱ ከባለሥልጣኑ በጽሑፍ ፈቃድ ሳያገኝ በዚህ መመሪያ መሠረት የተሰጠን ፈቃድ ማስተላለፍ ወይም ሌላ ሰው እንዲሰራበት መፍቀድ አይችልም፡፡

2) ባለሥልጣኑ ፈቃድ የሚተላለፍን ወይም ሌላ ሰው እንዲሰራበት የቀረበን ማመልከቻ በሚያይበት ጊዜ ለአዲስ ፈቃድ ማመልከቻ ተፈጻሚ የሚሆኑትን መስፈርቶችና ሁኔታዎች ከግምት ወስጥ ሊያስገባ ይችላል፡፡

3) ባለሥልጣኑ ማመልከቻውን በተቀበለ በሠላሳ (30) ቀናት ወስጥ ፈቃድ ለማስተላለፍ ወይም ሌላ ሰው እንዲሰራበት በቀረበው ማመልከቻ ላይ የሰጠውን ወሳኔ ከነምክንያቱ ለአመልካቹ ማሳወቅ አለበት፡፡

4) ባለፈቃዱ ፈቃዱን ለማስተላለፍን ወይም ሌላ ሰው እንዲሰራበት ማመልከቻ ሲያቀርብ በባለሥልጣኑ የሚፈለግበትን ማናቸውም ክፍያዎች መክፈል አለበት፡፡

## 39. የአክሲዮን ባለቤትነት ለውጥ

1) ማናቸውም የታቀዱ የፈቃድ ባለቤትነት፣ የውህደት ወይም ፈቃዱን የመቆጣጠር ለወጦች ቀደም የተያዘውን የአክሲዮኖች ባለቤትነትን የመቶኛ ድርሻ ከፍ የሚያደርገው የሆነ እንደሆነ ወይም አክሲኖቹ በማሻጣቸው ወይም በመተላለፋቸው ምክንያት (በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ) ሃያ አምስት (25) በመቶ ወይም ከዚያ በላይ የድምፅ ማስጠት ወይም አኮኖሚያዊ መብት የሚያሰጥ ከሆነ ባለፈቃዱ የባለሥልጣኑን ፈቃድ በቅድሚያ ማጠየቅ አለበት፡፡

2) ባለሥልጣኑ የወሳኔወን ምክንያቶች በመግለጽ መቀበሉን ወይም አለመቀበሉን የስምምት ጥያቄወን በተቀበለ በሠላሳ (30) የሥራ ቀናት ወስጥ ለባለፈቃዱ ማሳወቅ አለበት፡፡

3) ባለሥልጣኑ ፈቃዱን በባለቤትነት ማያዝ ወይም መቆጣጠር በዘርፉ የሚኖረወን የቴሌኮሚኬሽን ገበያን ወደ ተገቢ ያልሆነ ወድድር እንዲያመሩ የሚያደርግ መሆኑን ካረጋገጠ የአክሲዮን ባለቤትነት ለወጡን ወድቅ በሚድረግ ተቀባይነት ያላገኘበትን ምክንያት ለባለፈቃዱ ማሳወቅ አለበት፡፡

## ክፍል ስምንት

## ሥለ ሕግ ማክበር እና ማስፈጸም

### 40. ሕግ ስለማክበር

ባለሥልጣኑ ባለፈቃዱ የአዋጁን እና የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ማክበሩን መከታተል አለበት፡፡

### 41. ሕግ ስለማስፈጸም

1) ባለፈቃዱ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ከጣሰ ባለሥልጣኑ በዚህ መመሪያ፣ በአዋጁ እና በሌሎች ባለሥልጣኑ በሚያወጣቸው የህግ ማቀፍ ድንጋጌዎች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በአዋጁ አንቀጽ 52 መሠረት የሚወስዳቸው እርምጃዎች የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

ሀ) የገንዘብ መቀጮ ወይም ካሳ መስጠት፤ እና/ወይም፡

ለ) ፈቃድ ማገድ ወይም ማሰረዝ፡፡

2) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 33-35 እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ የሚወስዳቸው እርምጃዎች እና ቅጣቶች የሚኒስትሮች ምክር ቤት በአዋጁ አንቀጽ 52(6) መሠረት ፈቃድ ለማገድ ወይም ለማሰረዝ የሚያበቁ ሁኔታዎች እና ሌሎች አስተዳደራዊ ቅጣት የሚያስከትሉ የህግ መተላለፍ አይነቶች እንዲሁም የቅጣት ማጠን ለመወሰን በሚያወጣው ደንብ መሠረት አለበት፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 42. ከሌሎች የመንግሥት አካላት ፈቃድ ስለማግኘት

1) ባለሥልጣኑማናቸወንም የአገልግሎት መስጫ መገልገያዎች በማንኛወም ሜዳ ወይም የወሃ አካል ላይ፣ ወስጥ ለወስጥ ወይም በሥሩ ለማዘርጋት፣ ለማስቀመጥ፣ ለመትከል ወይም ለማጠገን የሌሎች የመንግሥት አካላትን፣ የአካባቢ ባለሥልጣናትን ወይም ሌሎች አግባብነት ያላቸወን ባለሥልጣናት ፈቃድ የማግኘት ኃላፊት አለበት፡፡

2) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባለሥልጣኑ ከሌሎች የመንግስት አካላት የተጠየቀወን ይሁንታ ለማረጋገጥ ድጋፍ መስጠት አለበት፡፡

### 43. በዚህ መመሪያ እና በፈቃድ ሁኔታዎች መካከል ስለሚኖር መቃረን

ማናቸወም የፈቃድ ሁኔታ ከዚህ መመሪያ ድንጋጌ ጋር የሚቃረን ሆኖ ከተገኘ፣ የመመሪያው ድንጋጌ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

### 44. የፈቃዶች መዝገብ

1) ባለሥልጣኑ፤

ሀ) በባለሥልጣኑ የተሰጡ የግል፣ የሚደብ እና የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ፈቃዶች፤ እና

ለ) የእያንዳንዱ ባለፈቃድ ስም እና የተመዘገበ አድራሻ፤

ማዝገብ ሜሪጀት እና ጠብቆ ማቆየት አለበት።

2) ባለሥልጣኑ በድረ-ገጹ ላይ የፈቃዶችን ማዝገብ ለሕዝብ ክፍት ወይም ተደራሽ ማድረግ አለበት፡፡

**45. ፈቃድን ለዋስትና ማስያዝ ስለማካልከሉ**

ከባለሥልጣኑ በቅድሚያ በጽሁፍ ፈቃድ ካልተሰጠ በስተቀር ባለፈቃዱ በዚህ መመሪያ መሠረት የተሰጠ ማንኛውንም ፈቃድ ለማቸውም ዓላማ ለሌላ ሰው መቡት ማጠት፣ በማዛሳት ማስያዝ ወይም በሌላ በማቸውም ሁኔታ በዋስትና ማስያዝ አይችልም፡፡

**46. ስለምደባና ዳግም ምደባ**

1) ባለሥልጣኑ በራሱ ወይም ከባለድርሻ አካላት ጋር በመማከር በዚህ መመሪያ የተማከቱትን የቴሌኮሚኬሽን አገልግሎቶችን ምደባ ወይም ዳግም ምደባ ማድረግ ይችላል፡፡

2) ምደባው ወይም ዳግም ምደባው የሚማከታቸው በሥራ ላይ ያሉ በባለሥልጣኑ የተሰጡ ፈቃዶች የፈቃድ ዘመናቸው እስከሚያበቃ ድረስ እንደፀኑ ይቆያሉ፡፡

3) ባለሥልጣኑ የተደረገውን ምደባ እና/ወይም ዳግም ምደባ ለሚማከተው የማንኛውም አገልግሎት ባለፈቃድ ስለሁኔታው በጽሁፍ ማስወቅ አለበት፡፡

4) ባለሥልጣኑ አንድን የቴሌኮሚኬሽን ፈቃድ፤

ሀ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ሥር በተማከቱት ምደቦች መሠረት እንዲመደብ ወይም ዳግም እንዲመደብ ሲወሰን፤ ለምደባው ወይም ለዳግም ምደባው ማስረት የሚሆነውን ምክንያት መወሰን አለበት፤ እንዲሁም

ለ) ውሳኔው ከሚማከታቸው ባለፈቃዶች ጋር የምክክር ስብሰባ ማካሄድ አለበት፡፡

**46. ያለፈቃድ ስለመሥራት**

1) የፀና ፈቃድ ሳይኖረው የቴሌኮሚኬሽን ኔትወርክ ሲያካሄድ እና/ወይም የቴሌኮሚኬሽን አገልግሎት ሲሰጥ የተገኘ ማንኛውም ሰው ለፈጸመው ጥሰት እና ባለሥልጣኑ ድርጊቱ እንዲቆም ትእዛዝ ከሰጠ በኋላ ለቀጠለው ለእያንዳንዱ ቀን ጥሰት አስተዳደራዊ የገንዘብ መቀጮ ይጣልበታል፡፡

2) በባለሥልጣኑ የተሰጠው ፈቃድ ዘመን ካበቃ በኋላ የቴሌኮሚኬሽን ኔትወርክ ሲያካሄድ እና/ወይም የቴሌኮሚኬሽን አገልግሎት ሲሰጥ የተገኘ ማንኛውም ሰው ፈቃዱ ሲወጣ ከሚከፈለው ክፍያ እኩል የሆነ አስተዳደራዊ የገንዘብ መቀጮ እና የፈቃዱ ዘመን ካበቃ በኋላ ለቀጠለው ለእያንዳንዱ ቀን ጥሰት ጥሰቶቹን በተማከተ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ መሠረት ተጨማሪ የገንዘብ መቀጮ ይከፍላል፡፡

**47. ማሻሻያ**

ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማንኛውም ጊዜ አስቀድሞ ለሁሉም ባለፈቃዶች በማስታወቅ እና በአዋጁ ድንጋጌዎች መሠረት የባለድርሻ አካላት የምክር ሂደት በማካሄድ ይህንን መመሪያ ማሻሻል ይችላል፡፡፡

**48. መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከ….. ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ …………ቀን 2013 ዓ.ም**

**ኢንጂነር ባልቻ ሬባ**

**የኢትዮጵያ ኮሚኬሽን ባለሥልጣን**

**ዋና ይሬክተር**

## አባሪዎች

### አባሪ ሀ፡ የግል ፈቃዶች ዝርዝር

1. የተጣሚ የቴሌኮሚኬሽን አገልግሎት ፈቃድ

2. የኢንተርኔት ማዞሪያ ሜከል ፈቃድ

3. ባለሥልጣኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንደ የግል ፈቃድ የሚወስነው ማንኛውም ሌላ ፈቃድ

### አባሪ ለ፡ የመደብ ፈቃዶች ዝርዝር

1. የኢንተርኔት አገልግሎት ሰጪ ፈቃድ
2. የዳታ ሜከል አገልግሎት ሰጪ ፈቃድ
3. የሆስቲንግ አገልግሎት ሰጪ ፈቃድ
4. የጥሪ ሜከል አገልግሎት ፈቃድ
5. የቴሌኮሚኬሽን ተጨማሪ አገልግሎቶች ፈቃድ
6. የመሠረተልማት አቅርቦትን ያላካተተ የኢንተርኔት አገልግሎት አቅርቦት ፈቃድ
7. የቪሳት አገልግሎት ፈቃድ
8. ዓለም አቀፍ የሳተላይት የግል ሞባይል ግንኙነት አገልግሎት ፈቃድ
9. የሳተላይት ዜናዎች ማሰባሰቢያ አገልግሎት ፈቃድ
10. የወስጥ የቴሌኮሚኬሽን መገልገያዎች ተከላ እና ጥገና ሥራዎች ፈቃድ
11. የውጭ የቴሌኮሚኬሽን መገልገያዎች ተከላ እና ጥገና ሥራዎች ፈቃድ
12. ባለሥልጣኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንደ የመደብ ፈቃድ የሚወስነው ማንኛውም ሌላ ፈቃድ

### አባሪ ሐ፡ ሌሎች ፈቃዶች

1) የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ፈቃድ
2) የመገናኛ ሬዲዮ ፈቃድ